ወት፡ ሐያው፡ የሚሆን፡ ሥጋ፡
፵፯ ተገኘ፨ መጀመሪያው፡ አዳም
ከመሬት፡ የተገኘ፡ መሬታዊ፡
ነው፡ ሁለተኛው፡ አዳም፡ ግን፡ ከ
ሰማይ፡ የመጣ፡ ሰማያዊ፡ ነው
፵፰ አዳም፡ መሬት፡ እንደሆነ፡ እንደ
ሱ፡ እኛም፡ መሬታውያን፡ ነን፡
ጌታም፡ ሰማያዊ፡ እንደሆነ፡ እ
ኛም፡ እንደሱ፡ ሰማያውያን፡
፵፱ ነን፨ መሬታዊ፡ አዳምን፡ እንደ
መሰልን፡ ሰማያዊ፡ ጌታን፡ እ
፶ ንመስላለን፨ ወንድሞቼ፡ በ
ሥጋዊ፡ በደማዊ፡ ሥራ፡ ያለ፡
ሰው፡ መንግሥተ፡ ሰማያትን
እንደይወርስ፡ እንነግራችኋለ
ን፡ የሚጠፋው፡ የማይጠፋው
ን፡ አይወርስም፨ ማቴ፡ ፲፯፡ ፲፯፡
፶፩ ዮሐ፡ ፩፡ ፲፫፨ እነሆ፡ የተሠወረ፡
ምሥጢር፡ እነግራችኋለሁ፡ ኢ
ኛ፡ ሁላችን፡ የምንሞት፡ አይደ
፶፪ ለንም፨ እንደ፡ ዓይን፡ ጥቅሻ፡ ፈ
ጥነን፡ እንለወጣለን፡ እንጂ፡ የ
ኋለኛው፡ ነጋሪት፡ በተመታ፡ ጊዜ
ሙታን፡ አካል፡ ሳይጎድልባቸ
ው፡ ይነሣሉ፡ እኛም፡ እንለወ
ጣለን፨ ማቴ፡ ፳፬፡ ፴፩፡ ፩፡ ተሰ፡ ፬
፶፫ ፲፮፨ ይህ፡ የሚጠፋው፡ የማይ
ጠፋውን፡ ይለብስ፡ ዘንድ፡ አለ
ውና፨ ይህ፡ የሚሞተው፡ የማ
ይሞተውን፡ ይለብስ፡ ዘንድ፡ አ
ለው፡ ፪ ቆሮ፡ ፭፡ ፬፨

፶፬ ይህ፡ የሚሞተው፡ የማይሞ
ተውን፡ በለበሰ፡ ጊዜ፡ ሞት፡ በመ
ቸነፍ፡ ተሰጠመ፡ ተብሎ፡ የተጻ
ፈው፡ ቃል፡ ያንጊዜ፡ ይፈጸማል
፶፭ ኢሳ፡ ፳፭፡ ፰፨ ሞት፡ ሆይ፡ ኃይል
ህ፡ ወዴት፡ አለ፡ መቃብር፡ ሆይ፡
ያንተስ፡ ማቸነፍ፡ ወዴት፡ አ
፶፮ ለ። ሆሴ፡ ፲፫፡ ፲፬፨ የሞት፡ ኃይሉ
ኃጢአት፡ ነው፡ የኃጢአትም
ኃይሏ፡ ኦሪት፡ ናት። ሮሜ፡ ፯፡
፶፯ ፲፬፡ ፯፡ ፲፬፨ ነገር፡ ግን፡ በጌታች
ን፡ በኢየሱስ፡ ክርስቶስ፡ ማቸነፍ
ን፡ ለእግዚአብሔር፡ ምስጋ
፶፰ ና፡ ይሁን፨ አሁንም፡ የተወደ
ዳችሁ፡ ወንድሞቻችን፡ የፀና
ችሁ፡ የተዘጋጃችሁ፡ ሁኑ፡ ከሃ
ይማኖትም፡ አትነዋወጡ፡ እ
ግዚአብሔርን፡ ለማገልገል፡
ሁልጊዜ፡ አብዝታችሁ፡ በጎ፡ ሰ
፶፱ ራ፡ ሥሩ፨ የደከማችሁት፡ ድካ
ም፡ በጌታችን፡ ዘንድ፡ ለከንቱ
እንደይደለ፡ ታውቃላችሁና፡
፪፡ ዜና፡ ፲፭፡ ፯፨ ምዕራፍ፡ ፲፮።

ለምእመናን፡ ስለሚወጣጣው፡ የአስተዋጽኦ
ገንዘብ፡ እሁድ፡ እሁድ፡ በየሳምንቱ፡ ገንዘቡን፡ እ
ንዲያወጣጡ፡ እንደ፡ አዘዛቸው፡ የተወጣጣውን
ም፡ ገንዘብ፡ ሁሉ፡ በየቤቱ፡ ይጠብቁ፡ ብሎ፡ እንደ፡ ጻፈላቸው

፩ ለምእመናን፡ ስለሚወጣጣው፡
ገንዘብ፡ ግን፡ በገላትያ፡ ያሉትን፡
ምእመናን፡ እንዳዘዝኋቸው
እናንተም፡ እንደዚሁ፡ አድርጉ

